ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረቢዕ አወል 30/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ኑቨምበር 5/2021 ግ.አ.

# የዒባዳ ግንዛቤ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**{إِنَّ اللَّهَ رَبِّي وَرَبُّكُمْ فَاعْبُدُوهُ هَذَا صِرَاطٌ مُسْتَقِيمٌ}**

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለታላቁ አላህ ይገባው፡፡የአንቀጹዋ ትርጉም

(«አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው፤ ስለዚህ ተገዙት፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው»)

ብቸኛ አጋር የሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ እንድሁም ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸው እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል

ዒባዳዎች (አገልግሎቶች) ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸውና ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ተግባራት ናቸው፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) ፍጥረታትን ከፈጠረባቸው አላማዎች ዋነኛዎቹ ናቸውም፡፡ ታላቁ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

**{وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنْسَ إِلَّا لِيَعْبُدُون}**

(ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡) እንዲሁም እንዲህ ይላል፡

**{وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلا نُوحِي إِلَيْهِ أَنَّهُ لا إِلَهَ إِلا أَنَا فَاعْبُدُون}**

(ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም፡፡)

እነሱም የሰው ልጅ እድሜ ልኩን ሊፈጽማቸው የሚገባው ሥራዎቹ ናቸው፡፡ ሐሰን አልበስሪ የተሰኙት የሃይማኖት ሊቅ (አላህ ምህረቱን ይችራቸውና) እንዲህ ይላሉ፡ «አላህ (ሱ.ወ.) ለሰው ልጅ ሥራ ከህለፈተ ሞት ሌላ ገደብ አላደረገለትም»

የእስልምና መመሪያ ህግጋትን የሚመራመር ሰው የዒባዳ ግንዛቤ ሁለት ፍችዎች ያሉት መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ አንደኛው ሰፊና አጠቃላይ ሲሆን እንደሲሳይ ማፈላለግ፣ መልካም ሥነ ምግባር፣ በወሬ ታማኝነት፣ ስህተተኛን ይቅር ማለት፣ ሰዎችን ማስታረቅ፣ የቤተሰብን ቀለብ መስፈርና ሌሎችንም እነዚህን የመሳሰሉትን ሁሉንም የደግ ነገርና የመልካም ሥራ መስኮች ያካትታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

**{لَّاخَيْرَ فِى كَثِيرٍ مِّن نَّجْوَاهُمْ إِلَّا مَنْ أَمَرَ بِصَدَقَةٍ أَوْ مَعْرُوفٍ أَوْ إِصْلَاحٍ بَيْنَ ٱلنَّاس وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ ٱبْتِغَاءَ مَرْضَاتِ ٱللَّهِ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا}**

(ከውይይታቸው በምጽዋት ወይም በበጎ ሥራ ወይም በሰዎች መካከል በማስታረቅ ከሚያዙ ሰዎች ውይይት በስተቀር በብዙው ውስጥ ደግ ነገር የለበትም፡፡ ይኸንንም (የተባለውን) የአላህን ውዴታ ለመፈለግ የሚሠራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ ( ሁሉም የሰው ልጅ አካላት ጸሐይ በምትወጣበት ቀን ሁሉ መጽዋት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ ከሁለት ሰዎች መካከል ፍትሃዊ ፍርድ መስጠቱ ምጽዋት ነው፡፡ አንድን ሰው በጭነት ከብት ላይ ጭነትን እንዲያወጣ ማገዙ ወይም በሱ ላይ እቃውን መጫኑ ምጽዋት ነው፡፡ መልካም ቃል መናገርም ምጽዋት ነው፡፡ ወደ ሶላት በሚያደርገው ጉዞ እያንዳንዱ እርምጃው ምጽዋት ነው፡፡ ከመንገድ አደናቃፊ ነገሮችን ማስወገድ ምጽዋት ነው፡፡

እንደዚሁም አዝርእትን በመዝራት፣ እንዱስትሪ በመመስረት፣ ጥቅሙ ለመላ ማህበረሰቡ የሆነንና ለሀገር እድገትና ብልጽግና ምክንያት የሚሆን ሥራን በጥራት በማከናውን ምድርን ማልማት አላህ (ዐ.ወ.) ከሚወዳቸው ዒባዳዎች አንዱና አላህ (ዐ.ወ.) ለሰው ልጅ ያስተላፈው ትእዛዝ ነው፡፡ ታላቁ አላህ እንዲህ ይላል፡

**{هُوَ أَنْشَأَكُمْ مِنَ الْأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا }**

(እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሰዎች መካከል አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጁ ለሰዎች ጠቃሚ የሆነ ሰው ነው፡፡ ከአላህ ዘንድ እጅግ የተወደደው ሥራ መከራን በማቃለል ወይም ጉዳዩን በማውጣት ወይም ከሱ ረሀብን

በማስወገድ በአንድ ሙእሚን መንስ ደስታን ማስገባት ነው፡፡ ከአንድ ወንድም ጋር ጉዳዩን ለማውጣት መጓዜን በዚህ መስጊድ -በመዲና መስጊድ- አንድ ውር ለዒባዳ ከመቀመጤ አብልጬ እወደዋለሁ፡፡ ቁጭቱን ለመወጣት ቢፈልግ ችሎታው እያለው ቁጭቱን አምቆ የያዘ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን ልቡን በደስታ ይሞለዋል፡፡ ከአንድ ወንድሙ ጋር ጉዳዩን ለማውጣት የሄደና ጉዳዩን ያወጣ ሰው እግሮች መቆም በሚያቅትባት የትንሳኤ እለት እግሮቹን ያረጋጋለታል፡፡)

ሁለተኛው የዒባዳ ግንዛቤ የተለየ ፍች የያዘ ሲሆን የእስልምና ስነ ስርኣቶችን መፈጸምና እንደ ስግደት፣ ምጽዋት መስጠት፣ ጾምና የሐጅ ሥራ ያሉ ማእዘናት አምልኮቶቹን ማከናወንን ያካትታል፡፡ ታላቁ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

**{حَافِظُوا عَلَى الصَّلَوَاتِ وَالصَّلَاةِ الْوُسْطَى وَقُومُوا لِلَّـهِ قَانِتِينَ}**

(በሶላቶች (በተለይ) በመካከለኛይቱም ሶላት ላይ ተጠባበቁ፡፡ ታዛዦች ኾናችሁም ለአላህ ቁሙ፡፡) እንዲሁም እንዲህ ይላል፡

**{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِنْ قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ}**

(እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡)

እንዲሁም እንዲህ ይላል፡

**{وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ وَمَا تُقَدِّمُوا لِأَنْفُسِكُمْ مِنْ خَيْرٍ تَجِدُوهُ عِنْدَ اللَّهِ}**

(ሶላትንም ስገዱ፡፡ ዘካንም ስጡ፡፡ ለአላህም መልካም ብደርን አበድሩ፡፡ ከመልካም ሥራም ለነፍሶቻችሁ የምታስቀድሙትን ሁሉ እርሱ የተሻለና በምንዳም ታላቅ ኾኖ አላህ ዘንድ ታገኙታላችሁ፡፡) እንዲህም እንዲህ ይላል፡

**{وَلِلَّهِ عَلَى النَّاس حِجُّ الْبَيْتِ مَن اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا وَمَنْ كَفَرَ فَإِنَّ الله غَنِيٌّ عَن الْعَالَمِينَ}.**

(ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡)

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

እዚህ ላይ የምናረጋግጠው ነገር ቢኖር ቅን ሰው ማለት አላህ ግድ ያደረጋቸውን እንስግደት፣ ጾም፣ ምጽዋት መስጠትና የሚችል ከሆነ ሐጅን እንደመፈጸም ያሉ ግዴታዎችን ከማከናወንና ዓለምን ከማልማት እንዲሁም በተሞገሱ ሥነ ምግባሮች መታነጽ መካከል ያለውን እንቅስቃሴውን ሚዛናዊ የሚያደርግ ሰው ነው፡፡

እንዲሁም ዒባዳዎች በልዩ ፍቻቸው በአንድ ሰው ልጅ ሥነ ምግባርና ጠባዩ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ካልሆነ በስተቀር በሚፈለገው መልኩ ፍሬያማ አይሆኑም የሚለውን ጉዳይ ማረጋገጥ እንወዳለን፡፡ ታላቁ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

(6)

**{ إِنَّ الصَّلاَةَ تَنْهَى عَنِ الفَحْشَاءِ وَالمُنْكَرِ}**

(ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለች፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (አንዳችሁ ጾም በሚይዝበት ቀን ጽያፍ አይናገር፡፡ ተገቢ ያልሆነ ቃልንም አይናገር)፡፡ እንዲሁም እንዲህ ይላሉ፡

(እኔ የተላኩትኮ የተሞገሱ ሥነ ምግባሮችን እንዲሞላ ነው)

በመልካም ምግባር የጨመረልህ ሰው የትክክለኛውን ሃይማኖት ግንዛቤ ይጨምርለሃል፡፡

ጌታችን ሆይ! አንተን እንዲናወድስና እንዲናመሰግን ላንተ ያለንን አገልግሎት እንዲናሳምር እገዛህን ስጠን፡፡